# የቅጥረኞች ድፍረት ልክ አለፈ!!

ታሪክን፣የአገርን ፍቅር ሳይፋቅ ሳይላጥ አምቃ ከትውልድ ትውልድ ያስተላለፈች የአገር ባለውለታ የሆነች የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ክብር የሚገባት ኢንስቲትዩት ነች። ግን ኢትዮጵያን ለማቀጨጭና ለመጣል መንገዱ፣ይህችን የታሪክ አምባ መናድ አስፈላጊና ወቅቱም አሁን ነው ብለው፣እነ አብይ አህመድ ስላመኑ፣ የጨበጡትን በጥፉትና በጭካኔ፣ደም የተነከረ ዱላቸውን ሰንዝረውባታል።

ቤተክርስያኒቱ እንድትናቅና እዚህ ድረስ እንድትዋረድ ያደረጓት፣ በየቤተክርስቲያኑና በየአጥቢያው የተሰገሰጉ ፋሽስት ካድሬ፣የእምነቱ መሪዎች ናቸው። አባ ጳውሎስን ያነሳ ፈጣሪ እነዚህንም ያንሳልን፣እረክስውና ወርደው እምነቱን ያስደፈሩ ይሁዳዎች ስለሆኑ፣ለተሸከሙት ከርሳቸው ሲሉ፣ ከቀላቢ አባዎራቸው ጋር፣እሬቻን እንደ ጅራፍ እዬጮሁ አብረው ያስተዋውቃሉ። የራሳቸው መስቀል በአል እንዳይከበር ተራራ የሚንድ ድንጋይ የሚፈነቅል ሰበብና ሸፍጥ በመደርደር እንዳይከበር ሲደረግ እምቢ ከማለት ይልቅ ስምምነት አድርገዋል።የበደል በደል ነው።

ግን እኔ የእምነቱ ተከታይ ባልሆንም የቤተክርስቲያኒቱ ታሪክ፣ ታሪኬ ነው ብዬ ስለማምን፣ በቤተክርስቲያኒቱ ላይ የሚደረግ ሴራና ደባ እቃወማለሁ፣ አምርሬ አወግዛለሁ። መጥፉት ካለበት መጤውና ግንድና ድንጋይ ቅቤ እየቀቡ የሚያመልኩት እሬቻና ገዳ እንደሆነ በኩራት እናገራለሁ።

አብዱ አሊ

2020/09/29